# የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምላሽ አሰጣጥን (የኮቪድ-19) አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

ባለፉት 24 ሰዓት ውስጥ በተደረገው ተጨማሪ 264 የላብራቶሪ ምርመራ ስምንት (8) ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል። በአጠቃላይ በሀገራችን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ሀምሳ ሁለት (52) ደርሷል። ከአንድ ኤርትራዊ በስተቀር ሁሉም ታማሚዎች ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ዝርዝር ሁኔታቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፣

| ተ.ቁ | ዜግነት | እድሜ | ፆታ | የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ | በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢትዮጵያዊ | 09 ወር | ወንድ | ከዱባይ የመጣና በለይቶ በማቆያ ውስጥ ያለ | ያለው |
| 2 | ኢትዮጵያዊ | 36 | ወንድ | ከዱባይ የመጣና በለይቶ በማቆያ ውስጥ ያሉ | ያለው |
| 3 | ኢትዮጵያዊ | 33 | ወንድ | ከዱባይ የመጣና በለይቶ በማቆያ ውስጥ ያሉ | ያለው |
| 4 | ኢትዮጵያዊ | 38 | ሴት | ከዱባይ የመጣና በለይቶ በማቆያ ውስጥ ያሉ | ያለው |
| 5 | ኢትዮጵያዊ | 25 | ወንድ | ከዱባይ የመጣና በለይቶ በማቆያ ውስጥ ያሉ | - |
| 6 | ኢትዮጵያዊ | 25 | ሴት | ከታይላንድ የመጣችና በለይቶ ማቆያ ውስጥ ያሉ | - |
| 7 | ኢትዮጵያዊ | 19 | ወንድ | የለውም | ያለው |
| 8 | ኤርትራዊ | 30 | ሴት | ከዩናይትድ ኪንደም ፣ ለንደን የመጣችና በለይቶ ማቆያ ውስጥ ያሉ | - |

በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 2271 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 264 |
| በዛሬው ዕለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 8 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 44 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 1 |
| ያገገሙ | 4 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 2 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 52 |

- የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከተለያዩ የአዲስ አበባና አዳማ የማህበረሰብ ክፍሎች የተወሰዱ 641 ናሙናዎች የላብራቶሪ ምርምራ ማከናወኑን እንዲሁም ከዚህ ቀደም በተለያዩ ቀናት በተሰጡ መግለጫዎች 609 የላብራቶሪ ውጤቶች በቫይረሱ የተያዘ ሰው አለመኖሩን ማሳወቃችን ይታወሳል። በተመሳሳይ የተቀሩት 32 ውጤቶች በዛሬው እለት በተደረገው ምርመራ በበሽታው የተያዘ ሰው አለመኖሩን አረጋግጧል።

ህብረተሰቡ የበሽታውን ስርጭት ግምት ውስጥ በማስገባት፡

- በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ግለሰቦች በአፋጣኝ በ8335 ወይም 952 በመደወል ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት እንዲያሳውቁ፣
- ለተለያዩ ጉዳዮች በአንድ ቦታ መሰባሰብ በማስወገድ፣ እጅን አዘውትሮ በመታጠብ፣ በአካል ንክኪ የሚደረግ ሰላምታን በመተውና አካላዊ መራራቅን ተግባራዊ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት እንዲከላከል እናሳስባለን፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ማግኘት ይቻላል፡

ዶ/ር ሊያ ታደሰ

የጤና ሚኒስትር

መጋቢት 29 ፣ 2012 ዓ.ም